- 11 -

ፍቅርማ ሞልቷል

በየካቲት ወር የማስታወቂያ ሰዎች አንድ ነገር እንድታስቡ ያደርጓችኋል። አየሩ ሁሉ በፍቅር እንደተሞላ...። ግና ፍቅራችንን ዓመቱን ሙሉ መግለጽ ነበረብን። ሆኖም ግን በዓመት አንድ ቀን ብቻ ተደረገለት። የፍቅረኞች (ቫላንታይን) ቀን ይሉታል ቀኑን። ሁሉም ሰው ያከብረዋል። ብዙዎች ዘንድ ከመከበሩ የተነሳ አንተንም ከማክበር ውጭ ምንም ምርጫ እንዳይኖርህ ያደርጉሃል። ያ ቀን ለቡቲክና ለቼኮሌት ነጋዴዎች ሰርግና ምላሻቸው ነውና። ያ ቀን በዓመት አንድ ጊዜ የሚመጣ ነው። በየካቲት ..

በዚህ ዙርያ ገባው "የፍቅረኞች ቀን" ጫጫታ በተሞላበት፤ ሳር ቅጠሉ ስለፍቅርና ተጣማሪነት በሚዘምርበት ቀን- እነርሱን ዝምብሎ መከተል እንጂ አንድም ሰው ቀን ስለተደረገለት ስለዚህ ፍቅር ምንነት የሚጠይቅበት ሁኔታ እምብዛም ነው። ያኔ ታዲያ አንድ ወሣኝ ጥያቄ ጭንቅላታችን ውስጥ ያቃጭላል።

እነኚህ ጥያቄዎች የሆነ ጊዜ አንዲት ጓደኛዬ ከፍቅረኛዋ ጋር በሆነች ጊዜ የሚሰማትን ስትነግረኝ የማስታውሳቸው ናቸው። ከርሱ ጋር ስትሆን - (በሷ አገላለፅ) ከርሱ ጋር ስትሆን መላው ዓለም ሁሉ ከፊቷ ጥፍት ይላል። እሱ ብቻ ነው የሚታያት። እሱ ነው ዓለሟ። እሷ በምትገልፅልኝ ነገር ላይ አስተያየት በሠጠሁ ቁጥር ጭራሽ ነገሩ እኔንም እየሳበኝ መጣ፤ የበለጠ እንድደነቅም አደረገኝ። ምን ዓይነት ፍቅር ነው! ... እላለሁ።

ሰው እንደመሆናችን መጠን በአፈጣጠራችን የፍቅር ስሜት እንዲሰማንና ወደ ሌሎች እንድንጣመር ተደርገን ነው። ይህ ሰዋዊ ተፈጥሮአችን ነው። ልንከደውና ልንደብቀው የማንችለው ነገር ነው። ግና የሚገርመው ነገር በዚህ ሁኔታ ውስጥ ስንሆን ስለ አንድ ሰው ብቻ እያሰብን፤ በቀን አምስት ጊዜ ጌታችንና ፈጣሪያችን ፊት ወደምንቆምበትና ከርሱ ጋር ወደምንገናኝበት መድረክ የምንገባበት ሁኔታ ነው። እንሰግዳለን። በአላህ (ሱ.ወ.) ፊት ቆመን እያለ መላው ዓለም እርባና ቢስ እንዴት ሊሆንብን እንደሚችል ሳስብ እጅጉን እገረማለሁ። እሱ ብቻ ሊታየን ሲገባ ሌላ ነገር እንዴት ይታየናል!!። ታዲያ በዚህ ሁኔታችን ለጌታችን ያለን ፍቅር በዚህ ምድር ላይ ካለ ከማንኛውም ነገር የሚበልጥ መሆኑን የመናገር ድፍረቱ አለን!?

አብዛኛውን ጊዜ የምናስበው አላህ (ሱ.ወ.) በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ብቻ የሚፈትነን መሆኑን ነው። ይህ ግን ትክክል አይደለም። እውነታው አላህ (ሱ.ወ.) በድሎትም ጭምር የሚፈትነን መሆኑ ነው። በፀጋዎች ይፈትነናል። የምናፈቅረውንና የምንፈልገውን ነገር በመስጠት ይፈትነናል። ብዙዎቻችን በዚህ ፈተና እንወድቃለን።የምንወድቀውም አላህ

(ሱ.ወ.) እነዚያን ነገራት ሲሰጠን ስጦታውን ወደምናመልከው ጣዖት በመቀየር ፊታችንን ወደነርሱ የምናዞር በመሆኑ ነው።

አላህ (ሱ.ወ.) ገንዘብ በመስጠት በፀጋው ሲባርከን ከርሱ በላይ የገንዘቡ ጥገኛ እንሆናለን። አቅምና ጉልበት የሆነን ገንዘቡ ሳይሆን ሰጪአችንና ለጋሻችን የሆነው አምላካችን መሆኑን እንዘነጋለን። ምንጩን ቸል ብለን ስጦታው ላይ እናተኩራለን።በድንገት በጉዟችን መሐል ሀሳብ እንቀይራለን። መጠጥ እና መሰል ሐራም ነገራትን መሸጥ፤ ለሥራ እንቅስቃሴያችን ብለን የተለያዩ ወለድ ያለባቸውን ብድሮች መበደር እንጀምራለን። ይህንን የምናደርገው የገንዘብ ደህንነት እንዲሰማን በማሰብ ነው። ድህነት እንዳይጠጋን። አስገራሚ በሆነ መልኩ በሞኝነታችን ስጦታውን ለመጠበቅ ስንል ሰጭውን መታዘዝ እናቆማለን። የሚገርም ነው!!።

አላህ (ሱ.ወ.) የምንወደውን ሰው በመስጠት ፀጋውን ሲቸረን፤ የዚህ ስጦታ ባለቤት ምንጭ አላህ (ሱ.ወ.)መሆኑን እንረሳለን። እና. . .አላህን ማምለክ በሚገባን ደረጃ አላህ የሰጠንን ሰው ማምለክ እንጀምራለን። ያንን ሰው የሕይወታችን ማዕከል እናደርገዋለን። ትኩረታችን፣ ሀሳባችን፣ ፍራቻችን እና ተስፋችን- የሚያጠነጥነው በዚያ ሰው ዙርያ ይሆናል። የትዳር አጋራችን ካልሆኑት ጋር ጭምር እነርሱን ለማግኘት ስንል ከነርሱ ጋር ሐራም ውሎ እንውላለን። ሐራም ነገር ላይ እንወድቃለን። የወደድናቸው ሰዎች ከተለዩን ደግሞ ሰማይ ሁሉ የተደፋብን ይመስለናል። በዚህ መልኩ አምልኳችንን ፀጋውን ከሰጠን አካል አላህ (ሱ.ወ.) ወደተሠጡን ነገሮችና ስጦታዎቹ እናዞራለን። አላህ የዚህ ዓይነት ሰዎችን እንዲህ ሲል ይገልፃቸዋል፡-

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَندَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ ٱللَّهِ ۖ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَشَدُّ حُبًّا لِّلَّهِ ۗ ﴾

«ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባላንጣዎችን (ጣዖታትን) አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ኾነው የሚይዙ አሉ። እነዚያ ያመኑትም አላህን በመውደድ (ከነርሱ) ይበልጥ የበረቱ ናቸው።» (አል-በቀራህ :165)

በዚህ መሰል የመጋረድ እና እይታን የማጣት ዝንባሌ ውስጥ ስንወድቅ እና አላህ (ሱ.ወ.) የዋለልንን ፀጋ እንዳናጣ ነው እንዲህ በማለት የሚያስጠነቅቀን። ለምሳሌ እንዲህ በማለት፡-

﴿ قُلْ إِن كَانَ ءَابَآؤُكُمْ وَأَبْنَآؤُكُمْ وَإِخْوَٰنُكُمْ وَأَزْوَٰجُكُمْ وَعَشِيرَتُكُمْ وَأَمْوَالٌ ٱقْتَرَفْتُمُوهَا وَتِجَٰرَةٌ تَخْشَوْنَ كَسَادَهَا وَمَسَٰكِنُ تَرْضَوْنَهَآ أَحَبَّ إِلَيْكُم مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَجِهَادٍ فِى سَبِيلِهِۦ فَتَرَبَّصُوا۟ حَتَّىٰ يَأْتِىَ ٱللَّهُ بِأَمْرِهِۦ ۗ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْفَٰسِقِينَ ﴾

«አባቶቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁ፤ ወንድሞቻችሁም ሚስቶቻችሁም፤ ዘመዶቻችሁም፤ የሰበሰባችኋቸው ሀብቶችም፤ መክሰሯን የምትፈሯት ንግድም፤ የምትወዷቸው መኖሪያዎችም፤ እናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልዕክተኛው፤ በርሱ መንገድም ከመታገል፤ ይበልጥ የተወደዱ እንደኾኑ፤ አላህ ትዕዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ።" በላቸው። አላህም አመፀኞች ህዝቦችን አይመራም።» (አት-ተውባህ :24)

ከላይ በቁርአን አንቀጹ የተገለጹት ሁሉ ለኛ ሐላል የተደረጉ ነገራት ናቸው። ልናፈቅራቸውና ልንወዳቸው ተፈቅዷልም። አንዳንዶቹ አላህ (ሱ.ወ.) በኛ ላይ ስለዋላቸው ጸጋዎች መገለጫዎች ናቸው።

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይለናል፡-

﴿ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَٰجًا لِّتَسْكُنُوٓا۟ إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم مَّوَدَّةً وَرَحْمَةً ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴾

«ለናንተም፤ ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን፤ ወደነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፤ በመካከላችሁም: ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፤ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ህዝቦች ተአምራት አልሉ።»(አር-ሩም :21)

በሌላ መልኩ ደግሞ አላህ (ሱ.ወ.) ከዚሁ ጸጋ ያስጠነቅቀናል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِنَّ مِنْ أَزْوَٰجِكُمْ وَأَوْلَٰدِكُمْ عَدُوًّا لَّكُمْ فَٱحْذَرُوهُمْ ۚ وَإِن تَعْفُوا۟ وَتَصْفَحُوا۟ وَتَغْفِرُوا۟ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴾

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከሚስቶቻችሁና ከልጆቻችሁ (ከአላህ መንገድ ስማስተጓጎል) ለናንተ ጠላቶች የሆኑ አልሉ፤ ስለዚህ ተጠንቀቋቸው፤ ይቅርታ ብታደርጉ ብታልፏቸውም፤ ብትምሯቸውም፤ አላህ በጣም መሓሪ አዛኝ ነው።» (አት-ተጋቡን :14)

በዚህ አንቀፅ ውስጥ ያለው ግሳፄና ማስጠንቀቂያ ከባድ ነው። የትዳር አጋሮቻችን እና ልጆቻችን የተጠቀሱት በይበልጥ የምናፈቅራቸው ለኛ የተለገሱ በረከቶች በመሆናቸው ነው። በጣም በምናፈቅራቸው ነገሮች ውስጥ ደግሞ ከባባድ የሆኑ ፈተናዎች አሉ። እነኚህን ፈተናዎች ማሸነፍ ማለት ከፊት ለሚጠብቀው ውብ ፍቅር ሲሉ በከባድ ማዕበል ውስጥ አሻግሮ ማራኪ አበቦችን መመልከት ማለት ነው። የዚህ ፈተና ተመጣጣኝ ክፍያው ይህ ነውና።

ምክንያቱም ከሁሉም በላይ አየሩ በፍቅር የተሞላ ነውና።

- 12 -

ፍቅር ማለት ይህ ነው!

ለሱ ሲሉ፤ ለሱን በመፈለግ ሂደት መላ ሕይወታቸውን የሚያሳልፉ ሰዎች ጥቂት አይደሉም። አንዳንዴ ይሠጣሉ፤ አንዳንዴም ይቀበላሉ። አንዳንዴ ደግሞ ያሳድዳሉ። ተከትለውት ይሮጣሉ። ግና ብዙን ጊዜ ደግሞ በመጠበቅ ነው የሚያሳልፉት። ፍቅር ማለት ከረጅም መንገድ በኋላ የሚደርሱበት ሥፍራ መሆኑን አምነው ተቀብለዋል። ግና ያ መንገድ እስኪያልቅ ድረስ መጠበቅና መታገስ አልቻሉም። የዚያ ዓይነቶቹ ልቦች በሌሎች ልቦች መንቀሳቀስ ምክንያት የሚንቀሳቀሱ ናቸው። እነዚያ ልቦች ተስፋ የሌላቸው አፍቃሪዎች፣ ለፍቅር ታሪኮች እጅ የሠጡ ልቦች ናቸው። የቱን ያህል ቢከብድም ለፍቅር ሲሉ እውነተኛውን መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆኑ ናቸው። ለነርሱ "መፈለግ" ማለት ሙሉ ሕይወታቸውን የሚያሳልፉበት ሥራ ነው። በርግጥም ይህ አሳዛኝ ፍለጋው አድካሚ ቢሆንም ግና ጥሩ ውጤትና መልካም ስጦታም ይኖረዋል።

የ"መጠበቅ" እና ለፍቅር ሲሉ በፍቅር የመውደቅ መንገድ እጅግ አሳማሚ መንገድ ነው። ቢሆንም ግን የራሱ የሆነ ትምህርት ሰጥቶ የሚያልፍ ነገር ነው። በመንገዱ ላይ ስለፍቅር ምንነት፣ ስለዚህች ዓለም ምንነት፣ ስለ ሰዎች፣ የአንድ ሰው ልብ ይህን ረጅምና ከባድ መንገድ እንዴት ማለፍ እንዳለበት እንማርበታለን። ብዙን ጊዜ ይህ መንገድ ፍቅርን ፈጣሪ ስለሆነው አምላክ ጭምር የራሱ የሆነ ትምህርት ይሠጠናል።

በዚህ መስመር ላይ ጉዞ የሚያደርጉ ሰዎች እነርሱ የሚፈልጉት ሰዋዊ ፍቅር ዋና ግብ አለመሆኑን በመጨረሻም ቢሆን ይገነዘባሉ። በርግጥ አንዳንዴ የዚያ ዓይነቱ ሰዋዊ ፍቅር ስጦታ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። ወደሚፈልጉበት ለመድረስ መንገድ ሲሆን ያለጊዜው እንዲያልቅ ሲደረግ ግን ውድቀት ሊያመጣ ይችላል። በዚህም የተነሳ ሙሉ ሕይወትን በተሳሳተ ግንዛቤ ውስጥ መኖር ሊመጣ ይችላል። ለቁሳዊ ነገር ብለን መስዋእት ሁሉ ልንከፍል እንችላለን። ፈጽሞ ሊሳካ ለማይችለውና ይህች ዓለም ለሌላት የፍፅምና ባህሪ ሙሉ ሕይወታችንን እንገብራለን።

ውሃ መስሎት ሲርብዱምን እየተከተለ የሚሮጥ ሰው መላ ሕይወቱን በሩጫ ይጨርሳል እንጂ ፈፅሞ ውሃው ላይ አይደርስም። እንዲሁ እንቅልፍ ብናጣ፣ ብናለቅስ፣ ብንደማ፣ የትኛውንም ውድ የሆነ ነገራችንን ክብራችንን ጭምር ብንሠጥ የዱንያ እርካታ ላይ ፈጽሞ ልንደርስባት አንችልም። ምክንያቱም እኛ የምንሮጥለት የምሉዕነት ጉዳይ የዚህች ዓለም ባህሪ ሆኖ አልተፈጠረምና። እኛ የምንፈልገው ፍጽምና በዚህ ቁሳዊ ዓለም አይገኝምና። ሊገኝ የሚችለው በአምላካችን ዘንድ ብቻ ነው።

የዚያ ዓይነቱ እኛ አልመነው የምንንቀሳቀስለት ሰው ፍቅር የበረሃ ላይ ቅዠት ብቻ ነው። ስለሆነም የምንፈልገው ይህ ከሆነ እስከመጨረሻው ድረስ ማሳደድ እንችላለን። ግና ከአሁን አሁን ደረስንበት ብለን ብናስበው እንኳ ፈጽሞ ልንደርስበት አንችልም። በአዕምሯችን የሳልነውን ነገር ፈጽሞ አናገኘውም።

ከዚሁ ቦታ ለመድረስ ስንል ሙሉ ሕይወታችንን ልንሠጥ እንችላለን። ይህን የምናደርገው የተነሳንለት ነገር ታሪክ መጨረሻው ያለው ስለሚመስለን ነው። ግና እዚያ ቦታ ከመድረሣችን በፊት ታሪካችን ያልቃል እንጂ አንደርስበትም። የሚያልቀውም በማግኘት፣ በመገናኘት፣ በጋብቻ ሊሆን ይችላል። ስኬቱ የሚገኘው በሁለቱ ነፍሶች (ወንድ እና ሴት) መገናኘት ብቻ ነው። ያኔ በዙርያችን ያለ ሰው ሁሉ ጉዞአችን እዚሁ ላይ እንዳበቃ እንድናስብ ሊያደርገን ይችላል። የነፍሳችንን አጋር፣ ግማሽ አካላችንን ባገኘንበት ቦታ ላይ። በቃ አሁን የተሟላን እንደሆነ አድርገው ይነግሩናል። ግን ይህ ፈጽሞ ውሸት ነው። ሙሉ እርካታና መሟላት የሚገኘው በአላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው።

ከትንሽነታችን ጀምሮ ከተለያዩ ታሪኮች፣ ዜማዎች፣ ፊልሞች፣ እና ሌሎች ነገሮችና አጋጣሚዎች የወሰድናቸው ትምህርቶች ሁሉ የነገሩን ነገር ቢኖር የጋብቻ ሕይወት በጀመርን ጊዜ የተሟላን እንደምንሆን ነው። ምሉዕነትን ከጋብቻ ጋር ስለምናያይዝ አላህ (ሱ.ወ.) ካልፈቀደው ወይም ከጠላን ማግባት ካልቻሉት መካከል እንሆናለን፤ ወይ ደግሞ እንፋታለን - የሚል ሀሳብ ሁሉ ይኖረናል። በዚህም የተነሳ በአንድ በኩል የጎደለንና ያልተሟላን እንሆናለን .. ብለን እናስብ ነበር።

ለረጅም ዘመን የተማርነው ነገር የህልማችን ታሪክ የሚያበቃው ስናገባ እንደሆነ ነው። ጋብቻም የጀነት ኑሮ መጀመርያ እንደሆነ ነው። በዚህም ምክንያት መቼ እንደምንድንና እንደምንሟላ፣ የሆነ ጊዜ የተሰበረብን ነገር ሁሉ መቼ እንደሚጠገንልን እናስብ እንብሰለሰል ነበር። ችግሩ ግን ታሪኩ እዚያ ላይ የሚያበቃ አለመሆኑን ነው። ባይሆን የሚጀምረው እዚያ ነው። ግንባታ ከዚያ ነው የሚጀምረው። የሕይወት ግንባታ። የስብእናና የመልካም ባህሪ ግንባታ። የትዕግስት ግንባታ። የመቻል፣ የፅናት እና የመስዋእትነት ግንባታ። ራስን የመቻል ግንባታ። የፍቅር ግንባታ።

መንገዳችንን መገንባት የምንጀምረው ከዚህ ነው። መገንባት ማለት ወደርሱ መንገድ መመለስ ነው። ወደ አላህ (ሱ.ወ.) መንገድ።

ልናገባው የምንፈልገው ሰው የሕይወታችን ዋና ግብ ከሆነ፤ ትግላችን አሁን ገና ነው የተጀመረው ማለት ነው። በዚህን ጊዜ ሚስታችን/ባላችን ትልቅ ፈተና ይሆኑብናል። ያንን ሰው አምላካችን መቀመጥ ከነበረበት ቦታ ከልባችን እስካላወጣን ድረስ። ካላስወጣነው የጉዳት ጊዜው ማቆሚያ አይኖረውም ይቀጥላል። የትዳር ጓደኛችን በራሱ/ሷ የጉዳታችን

ምክንያት ይሆናል/ትሆናለች። ሰውን እና አምላክን ማስቀመጥ ያለብን ቦታ ለይተን እስካላወቅን ድረስ ፈተናው ከባድ ነው የሚሆነው። የሰውን ለሰው፤ የአምላክን ለአምላክ ማድረጉ ነው ተገቢው አኗኗር።

በዚህ ጉዞ ወቅት ከምንማራቸው ነገሮች መካከል ከረጅም ጊዜ ማጣት፣ ማግኘት፣ መውደቅ፣ መነሳት እና በርካታ ስህተቶች በኋላ በትንሹ ሁለት ዓይነት ፍቅር መኖሩን እንረዳለን። ለምሳሌ - አንዳንድ ሰዎችን ከነርሱ በምናገኛቸው ነገሮች ምክንያት እንወዳቸዋለን። የሚሠጡን ነገር ነው ለነርሱ ያለንን ቅርበት እንድንወስን የሚያደርገን። የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ አብዛኛው የፍቅር ዓይነት ነው። ፍቅር ዘላቂ እንዳይሆን ከሚያደርጉት ነገሮች መካከልም አንዱ ይህ ነው። የሰው ልጅ የመስጠቱ ሁኔታ ወጥ አይደለም፤ በየጊዜውና ሁኔታው ተቀያያሪ ነውና። በዚህም የተነሳ የኛም ምላሽ በመስጠት ሁኔታው ላይ የተመሠረተ ነው የሚሆነው። ምላሾችንና ውለታዎችን የምንከተል ከሆነ ደግሞ ያንን ሁኔታ ስናሳድድ ነው የምንኖረው። ለዚያ ሰው ወጥ የሆነ ስሜት አይኖረንም። በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ላይ ጥገኛ የሆነ ፍቅር ወጥነት አይኖረውም። ከሁኔታዎችና ከአቀራረቦች ጋር የሚለዋወጥ ነው የሚሆነው። በተከተልነው ቁጥር ደግሞ ሸሽቱ የባሰ ነው የሚሆነው። ስለሆነም እንደተከተልነው እንኖራለን እንጂ አንደርስበትም። አንጨብጠውም።

ግና አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ሳይታሰብ ወደ ልባችን ይገባሉ። እንወዳቸዋለን። የምንወዳቸውም ለሚሠጡን እና ለሠጡን ነገር ሳይሆን በነርሱነታቸው እና በማንነታቸው ብቻ ነው። በነርሱ ውስጥ የምናየው ውበት የፈጣሪያችን ነፀብራቅ ሆኖ ይታየናል። ስለዚህም እንወዳቸዋለን። ስለሆነም ከነርሱ የምናገኘው ነገር ሳይሆን የምንሠጣቸው ነገር ነው የሚያስደስተንና እነርሱን የሚያስወድደን። የዚህ ዓይነቱ ፍቅር ከራስ በላይ የሆነ፤ ከራስ ወዳድነት ያለፈ ነው። ይህ ሁለተኛ ላይ የጠቀስነው ፍቅር አይገኝም፤ ቢኖርም እምብዛም ነው። በተለይ በዚህ ዘመን። በሆነ ነገር ላይ ካልተመሠረተ፣ የሆነን ጥቅም ካላሰበ፣ ከአላህ ፍቅር ጋር ካልተጋጨ ትልቅ ደስታን የሚሠጥ ፍቅር ነው የሚሆነው የዚህ ዓይነቱ ፍቅር። ያም ሆነ ይህ በሁሉም መልኩ መውደድ ስንል ባህሪው መፈለግ ነው፣ ጥገኛ መሆን ነው፣ መጠበቅ ነው። የስቃይ እና የውድቀት ንጥረ ነገሮች የተሞሉበት ነው።

ስለሆነም መላ ሕይወታቸውን ፍቅርን ፍለጋ የደከሙ ሁሉ መገንዘብ ያለባቸው ነገር የየትኛውም ነገር ንፅህና የሚገኘው ከመነሻው እና ከዋና ከምንጩ እንደሆነ ነው። እውነተኛ ፍቅርን የምትፈልጉ ከሆነ በአላህ (ሱ.ወ.) በኩል ፈልጉ። በሱ የፍቅር ምንጭ ላይ ያልተመሠረተ ማንኛውም ነገር ጠጪውን ይመርዛል እንጂ አይፈውሰውም። ከሱ ምንጭ ውጭ መጠጣትን ያዘወተረ ሰው ሲጠጣ ከኖረ በኋላ በመጨረሻም ከዚያ ምንጭ በጠጣው መርዝ መሞቱ አይቀርም። በሂደት ነው ውስጡ የሚሞተው:: በመጨረሻም የሚጠጣው ንፁህ የውሃ ምንጭ እስኪያጣ ድረስ።

በዙርያችሁ የምትመለከቱትን ውብ ነገር ሁሉ የአምላካችሁን ውበት ማሳያ አድርጋችሁ እስካሰባችሁ ድረስ በትክክለኛው መንገድ መውደድን ትማራላችሁ። ስለሱ ብላችሁ ትወዳላችሁ። ማንኛውንም ነገርም ሆነ ሰው ስትወዱ ለሱ እና ስለሱ ብላችሁ ብቻ ነው የሚሆነው። የዚያ ዓይነቱ ፍቅር መሰረት አላህ ነው።

እንዲያ ሲሆን የያዛችሁት ነገርም ቋሚ ሆኖ ይታያችኋል፤ ደመነፍሳዊ ስሜት አይሆንባችሁም። የምታሳድዱት ነገርም ጊዜያዊና አላቂ ነገር አይሆንም። ያላችሁ ነገርና ለማግኘት የምታስቡት፣ የወደዳችሁትና ምትወዱት ሁሉ አላህ ነው የሚሆነው። እሱ ብቻ ነው ዘላለማዊ እና የማይቀየር። እሱን ብላችሁ ስትንቀሳቀሱ ለርሱ ብቻ ብላችሁ የምትሠሩ ነው የምትሆኑት። ለርሱ ብቻ ብላችሁ የምትሠጡ፣ የምትቀበሉ፣ የምትወዱ፣ የምትጠሉ ነው የምትሆኑት። ለራሣችሁ ስሜት ብላችሁ የምታደርጉት ነገር አይኖርም። ለሱ ብቻ ነው፤ ለራሣችሁ ጥቅም አይደለም።

ይህ ማለት እርሱ የወደደውን ነገር ትወዳላችሁ። እርሱ የጠላውን ነገር ትጠላላችሁ። ስትወዱ ለአላህ ብላችሁ እንጂ ውለታ አስባችሁ አይደለም የሚሆነው። ስለወደዳችሁ ለወደዳችሁት ትሠጣላችሁ። የምታደርጉትን ነገር ያደረጋችሁት ለአላህ ነው። ምላሹን ከሠጣችሁት ሰው ሳይሆን ለሱ ብላችሁ ከሠጣችሁት አላህ ነው የምትጠብቁት። ለአላህ ብላችሁ ትብቃቃላችሁ። በአላህ ብቻ የተብቃቃ ሰው ከአላህ አገኛለሁ ብሎ የጠበቀ ሰው ከሱ በላይ ሀብታም እና ሌሎች ዘንድ የበለጠ ተወዳጅ የለም። ውዴታችሁ በአላህ፣ ለአላህ እና ስለ አላህ ነው። ይህ ሁኔታ ከራስ ነፍስ ባርነት ነጻ የመውጣት ምልክት ነው። ይህ ነው ነፃነት። ይህ ነው ደስታ ማለት።

ይህ ነው እውነተኛ ፍቅር ማለት።